# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ቢሮ

# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሞተር ብስክሌት ፈቃድና ቁጥጥር አሰራር መመሪያ ቁጥር 42/2013

ሰኔ 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## መግቢያ

አዲስ አበባ የሀገራችን ርዕሰ ከተማና የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ማዕከል ብሎም የአፍሪካ እና የተለያዩ አገራት ኢምባሲዎችና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች መቀመጫ ናት። በመሆኑም በከተማችን ያለው ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴ የተሳለጠ እንዲሆን የከተማው ትራንስፖርት ጉልህ ሚና አለው። ስለሆነም የከማችን የትራንስፖርት ስርዓት ከተማዋ ላለችንበት እድገትና ላላት ዓለም አቀፍ ቦታ በሚመጥን ደረጃ እያደገ ያለ ሲሆን በየጊዜዉ ለሚነሱ ማህበረሰባዊ ጥያቄዎች መመለስ የሚያስችሉ አሰራሮች መዘርጋትም ያስፈልጋል።

በአሁኑ ሰዓት በከተማችን ካለው የትራንፖርት ፖሊሲ በተቃራኒ እያደገ የመጣዉ የሞተረ ብስክሌት ትራንስፖርት ስርዓት የተለያዩ ማህበረሰባዊ ችግሮች እያስከተለ ይገኛል። በከተማችን ያለዉ መሰረተ ልማት ከሞተርብስክሌቶች ፈጣንና ተለማጭ እንቅስቃሴ አንፃር አመቺ ያልሆነና ለአደጋ የተጋለጠ ነው። በመሆኑም ከሞተር ብስክሌቶች ቁጥር መጨመር ጋር ተያይዞ የትራፊክ አደጋዎች መጨመር በተለይም ተገቢውን የመንገድ ደህንነት መርሆዎች እና ህግ ተከትለው ስለማያሽከረክሩ እንዲሁም ከፍጥነታቸው እና ከመጠናቸው ማነስ የተነሳ በሌሎች ተሽከርካሪዎች እይታ ስር ስለማይወድቁ ለአደጋ እየተጋለጡ ይገኛሉ። አደጋ ሲከሰትም የመትረፍ እድላቸው ዝቅተኛ ከመሆኑም ባለፈ ቢተርፉም ለከፍተኛ የአካል ጉዳት ስለሚዳረጉ ለከፍተኛ ስነልቦናዊና ማህበራዊ ጉዳት ይዳረጋሉ። የሞተር ብስክሌት አሽከርካሪዎች እራሳቸውን ለአደጋ ያጋለጡ ከመሆናቸውም ባለፈ ከዋናው የተሽከርካሪ መንገድ በመውጣት በእግረኛ መንገዶች ላይ እየተሽለኮለኩ ለማሽከርከር በሚያደርጉት ህገወጥ ተግባር እግረኞችን ለአደጋ እያጋለጡ በመሆኑ፣

ሞተር ብስክሌቶች ለግል አገልግሎት ከመዋል ያለፈ በህዝብ ትራንስፖርት ለመሰማራት የሚስችል አሰራር የሌለ ቢሆንም በተለያዩ የከተማዋ አካባቢዎች በህገወጥ ትራንስፖርት ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ሲሆን በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ ቁጥጥር ሂደትም በመጠን ትንሽ ከመሆናቸው፣ በከፍተኛ ፍጥነት የሚንቀሳቀሱና በፍጥነት መቆጣጠሪያ ራዳርም ጭምር በቀላሉ የማይያዙ በመሆናቸው እንዲሁም ህግን አክብረው ለተቆጣጣሪው አካል ለመታዘዝ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው የተነሳ እርምጃ ለመውሰድ ችግር እየፈጠሩ በመገኘታቸው፣

በከተማችን ውስጥ ምንም እንኳ የኮድ **2** ሞተር ብስክሌቶች ምዝገባ ማካሄድ የተቋረጠ ቢሆንም ከሌሎች ክልሎች ምዝገባ በማካሄድ ወደ ከተማችን የሚገቡ የሞተር ብስክሌቶች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ ሲሆን ከሌሎች ተሽከርካሪዎች እድገት አንፃር ሲታይ በሁለት እጠፍ እድገት እያሳየ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ። ይህም በከተማዋ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ላይ ስጋቶችን እና ተጨባጭ ችግሮችን እየፈጠረ በመሆኑ፣

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሞተር ብስክሌቶች በመጠቀም በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በገበያ ማዕከላት፣ በትምህርት ቤቶችና የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት አካባቢ የሚደረግ ዘረፋና ስርቆት እንዲሁም ህገ-ወጥ ድርጊቶችን የመፈፀም ዝንባሌ እየተበራከተ በመምጣቱ የተነሳ በዜጎች ላይ እተፈጠረ ያለውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ስነ-ልቦናዊ መታወክ ለመከላከል የሚያስችሉ ስራዎች በመንግስት በኩል መሠራት ያለባቸው በመሆኑ፣

የከተማችን የትራንስፖርት አገልግሎት የበለጠ ተወዳዳሪ ደህንነቱ የተጠበቀና ብቃት ያለው ሆኖ እንዲራመድ ተገቢው ክትትልና ድጋፍ የሚጠይቅ በመሆኑ እንዲሁም የከተማውን የትራንስፖርት አገልግሎት በማዘመን የትራፊክ



City Government of Addis Ababa Road and Transport Bureau

ማኔጅመንት ስራውን ለማቀላጠፍ እንዲቻል በአዲስ አበባ ከተማ የሞተር ብስክሌቶች እንቅስቃሴን በመወሰን የፈቃድና ቁጥጥር አሰራርን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 3 ፊደል ተራ (ረ) እና (ሰ) ድንጋጌዎች መሠረት የህዝብን ደህንነት የሚጎዱ ተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ በተመለከተ ማገድ እንዲሁም ከተሞቹ የትራንስፖርት አገልግሎት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች ተግባራት ማከናወን እንዲችሉ የፌዴራል የትራንስፖርት ባለስልጣን የውክልና ስልጣን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰጠው በመሆኑ፣

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራንስፖርት ቢሮ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፣ ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 64/2011 አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀፅ 3(ሠ) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ *"የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሞተር ብስክሌት ፈቃድና ቁጥጥር መመሪያ ኣሰራር ቁጥር 42/2013"* ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

2.1. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

2.2. **"አስተደዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

2.3. **"ቢሮ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ነው፤

2.4. **"ኤጀንሲ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ ነው፤

2.5. **"ባለስለልጣን"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፤

2.6. **"መንገድ"** ማለት ተሽከርካሪዎችና እግረኞች በተለምዶ የሚጠቀሙበት ማናቸውም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚገኝ መንገድ ወይም መተላለፊያ ነው፤

2.7. **"ፈቃድ"** ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት በከተማው የአስተዳደር ወሰን ክልል ውስጥ ለመንቀሳቀስ በባለስልጣኑ ፈቃድ ስለመሰጠቱ የሚያመለክት መረጃ የያዘ ሰነድ ነው፤

2.8. **"ፈቃድ ሰጪ አካል"** ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት የባለሁለት ሞተር ብስክሌት በከተማው ውስጥ ለመንቀሳቀስ ፈቃድ እንዲሰጥ ስልጣን የተሰጠው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፤

2.9. **"ሞተር ብስክሌት"** ማለት የጎን ተሽከርካሪውን ሳይጨምር ክብደቱ ከ 400 ኪሎ ግራም የማይበልጥ ባለሁለት ጎማ ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤

2.10. **"ድርጅት" ማለት** በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ማንኛውም መንግስታዊ ወይም መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ወይም ተቋም ነው፤

2.11. **"ትራፊክ ተቆጣጣሪ"** ማለት የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ እና የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መከበራቸውን ለመቆጣጠር እና የትራፊክ ፍሰትን ለማስተናበር አግባብነት ባለው ሕግ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ሲሆን ትራፊክ ተቆጣጣሪ ፖሊስ እና የትራንስፖርት ተቆጣጣሪ ተብሎ ይከፈላል"፤

2.12. **"ትራፊክ ተቆጣጣሪ ፖሊስ"** ማለት የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ እና የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መከበራቸውን ለመቆጣጠር እና የትራፊክ ፍሰትን ለማስተናበር አግባብነት ባለው ሕግ ሥልጣን የተሰጠው የፖሊስ አባል ነው"፤

2.13. **"ትራንስፖርት ተቆጣጣሪ"** ማለት የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ እና የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መከበራቸውን ለመቆጣጠር በተለይም በመንገድ ላይ የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎችን የቴክኒክ ብቃት እንዲያረጋግጥና ከትራንስፖርት አስተዳደር ጋር በተያያዘ የወጡ መመሪያዎችን አፈፃፀም ለመቆጣጠር አግባብ ባለው አካል ሥልጣን የተሰጠው ሰው ነው፤

2.14. **"የአደጋ አገልግሎት ተሽከርካሪ"** ማለት የአደጋ አገልግሎት ተግባሩን ለመፈፀም በሚዘዋወርበት ወቅት በግንባሩ አቅጣጫ ሳያቋርጥ ብልጭ ብልጭ የሚል ቀይ ወይም ሰማያዊ የመብራት ምልክት የሚያሳይ ወይም ለማስጠንቀቂያ ተስማሚ የሆነ ድምፅ ምልክት ወይም ደወል የሚያሰማ አምቡላንስ፣ የመከላከያ ወይም የፖሊስ ኃይል ወይም የእሳት አደጋ መከላከያ ተሽከርካሪ ነው፤

2.15. **"ብራንድ"** ማለት አንድን ተቋም ወይም ድርጅት በተለየ መልኩ የሚገልፅ የቀለም ቅብ እና ስዕላዊ መግለጫ ማለት ነው፤

2.16. **"አርማ"** ማለት አንድን ድርጅት ወይም ተቋም በልዩ ሁኔታ የሚገልፅ ስዕላዊ ምልክት ወይም ፅሁፍ ሆኖ በሚመለከተው የመንግስት አካል ህጋዊ እውቅና ያለው ነዉ፤

2.17. **"ዩኒፎርም"** ማለት የአንድን ተቋም ወይም ድርጅት ሞተር ብስክሌት አሽከርካሪ በተለየ መልክ የተዘጋጀ ሙሉ ልብስ ነው፤

2.18. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ወደ አዲስ አበባ ከተማ ክልል በሚገቡና በከተማ ውስጥ በሚንቀሳቀሱ እንዲሁም ከተማዋን አቋርጠው እየተሽከረከሩ በሚያልፉ ማናቸዉም ሞተር ብስክሌቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## ስለ ሞተር ብስክሌት የእንቅስቃሴ ወሰን

4. ማንኛውም ባለሁለት ጎማ ሞተር ብስክሌት በከተማው መንገድ ላይ በማንኛውም ቀንና ሰዓት እንዳይንቀሳቀስ ታግዷል።

5. የአንቀፅ 4 ድንጋጌ ቢኖርም ይህ መመሪያ፤
   - 5.1. የሀገር መከላከያ እና ሌሎች የፀጥታ አካላት ንብረት የሆኑ የእነዚህን አካላት ስራ የሚሰሩ ሞተር ብስክሌት፤
   - 5.2. በህግ መሠረት የድንገተኛ አደጋ ተሽከርካሪዎች ተብለው የተለዩ አካላት ንብረት የሆኑና የእነሱን ስራ የሚሰሩ ሞተር ብስክሌት፤
   - 5.3. የከተማ አስተዳደሩ የትራንስፖርት ተቆጣጣሪ እና ህግ አስከባሪ አካላት ንብረት የሆኑ ሞተር ብስክሌት፤
   - 5.4. ለአካል ጉዳተኛ ተብሎ በተለይ የተሰራ እና አካል ጉዳተኛ የሚጠቀምበት ሞተር ብስክሌት፣ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

6. የአንቀፅ 4 ድንጋጌ ቢኖርም በንዑስ አንቀፅ **5.1.** እና **5.2.** መሠረት በከተማው መንገድ ላይ እንዲንቀሳቀሱ የሚፈቀድላቸው ሞተር ብስክሌት አሽከርካሪዎች ሲንቀሳቀሱ የድርጅቱ አርማ ያለበት የደንብ ልብስ መልበስ ይኖርባቸዋል።

7. የአንቀፅ 4 እና 5 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ኤጀንሲው እና በአዲስ አበባ ከተማ የትራንስፖርት ባለስልጣን እያንዳንዱ የግል ይሁን የማህበር ሞተር ብስክሌት መቆጣጠር የሚያስችል ቴክኖሎጂ የገጠሙ ፍቃድ ሊያገኙ ይችላሉ።

8. በአንቀፅ 7 የተቀመጠዉን ድንጋጌ ቢሮው በሚያወጣቸው ዝርዝር አሰራርና የቴክኖሎጂ ምርጫዎች የሚወሰን ይሆናል።

9. የአንቀፅ 4 እና 5 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው እንዳስፈላጊነቱ ኤጀንሲው ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ መሆኑን ሲያምንበት ፈቃድ ሳያስፈልጋቸው በከተማው መንገድ ላይ ሊንቀሳቀሱ የሚችሉ ሌሎች ሞተር ብስክሌት አይነት በመወሰን ለባለስልጣኑ ሲያሳውቅ ያለ ፈቃድ እንዲንቀሳቀሱ ሊያደርግ ይችላል።

10. የዚህ መመሪያ አንቀፅ 4 ድንጋጌ ቢኖርም፤
    - 10.1. የድርጅት ንብረት የሆነ ሞተር ብስክሌት፣
    - 10.2. የአለም አቀፍ ድርጅት፣ የኤምባሲ፣ የቆንስላ ጽህፈት ቤት ንብረት የሆነ ሞተር ብስክሌት፤
    - 10.3. የሐይማኖት ተቋማት፣ ሲቪክ ማህበር ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅት ንብረት የሆነ ሞተር ብስክሌት፤
    - 10.4. የአንቀፅ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከአገልግሎታቸው አንፃር እየታዩ በኤጀንሲው የበላይ አመራር ውሳኔ በባለስልጣኑ ፈቃድ የሚሰጠው ሞተር ብስክሌት በከተማው መንገድ ላይ መንቀሳቀስ ይችላል።

## ክፍል ሶስት

## ስለ ፈቃድ አሰጣጥ

11. **ፈቃድ ማግኘት አስፈላጊ ስለመሆኑ**

በከተማው የአስተዳደር ወሰን ክልል ውስጥ በሚገኝ መንገድ ላይ ለመንቀሳቀስ የሚፈልጉ በዚህ መመሪያ ከአንቀፅ 5 እስከ አንቀፅ 10 ስር የተጠቀሱ አካላት ፈቃድ እንዲሰጣቸው በጽሁፍ አመልክተው ከባለስልጣኑ ፈቃድ ሳያገኙ ሞተር ብስክሌታቸውን በከተማው መንገድ ላይ ማንቀሳቀስ አይችሉም።

12. **ፍቃድ ሊጠይቁ ስለሚችሉ አካላት**

በዚህ መመሪያ ከአንቀፅ 5 እስከ 10 መሰረት የፈቃድ ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው የተቋሙ ወይም የድርጅቱ ህጋዊ ተወካይ ነው።

13. **ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች**

ፈቃድ ለማግኘት የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው፤

13.1. ከፈቃድ ጠያቂው ተቋም ወይም ድርጅት የተፃፈ ደብዳቤ እና ጉዳዩን ለማስፈፀም ውክልና የተሰጠው ሰው፣

13.2. ባለስልጣኑ የሚያዘጋጀው ቅፅ ሞልቶ ማቅረብ፣

13.3. ፈቃድ የተጠየቀለት ሞተር ብስክሌት ሰሌዳ ቁጥር እና ሊብሬ ኮፒ፣

13.4. የታደሰ የንግድ ፈቃድ ወይም የምዝገባ የምስክር ወረቀት፣

13.5. ፈቃድ በሚጠየቅላቸው ሞተር ብስክሌቶች ላይ የድርጅቱን ሎጎና ብራንድ በመቀባት መቅረብ የሚችል፣

13.6. ሞተር ብስክሌቱ ለህጋዊ አላማ ብቻ እንደሚውል ባለስልጣኑ ባዘጋጀው ግዴታ መግቢያ መግለጫ ላይ ስምምነት የሚፈርም፣

13.7. የሞተር ብስክሌቱን ሰሌዳ በሪሺት አስሮ ማቅረብ፣

13.8. በባለስልጣኑ የሚጠየቀውን የአገልግሎት ክፍያ መክፈል።

14. **ፈቃድ ስለመስጠት**

14.1. በዚህ መመሪያ መሰረት በከተማው መንገድ ላይ ሞተር ብስክሌት ለማንቀሳቀስ የተፈቀደለት ሰው በባለስልጣኑ ፈቃድ ይሰጠዋል፤

14.2. ፈቃዱ የሚከተሉትን ነጥቦች የያዘ መሆን አለበት፤

ሀ. ፈቃድ የተሰጠው ተቋም ወይም ድርጅት ሙሉ ስምና አድራሻ በዝርዝር፣

ለ. የሞተር ብስክሌቱ የሻንሲ ቁጥር፣ የሞተር ቁጥር እና የሰሌዳ ቁጥር፣

ሐ. ፈቃዱየሚያበቃበት ቀን፣

መ. የፈቃድ ሰጪው አካል ማሕተም እና የሚመለከተው ኃላፊ ፊርማ።

15. **ስለ አገልግሎት ክፍያ**

በዚህ መመሪያ መሠረት ለሚሰጠው አገልግሎት **ብር 300.-** (ሦስት መቶ ብር) የአገልግሎት ክፍያ የከፈላል።

16. ፈቃድ ስለሚቆይበትጊዜ

በዚህ መመሪያ መሠረት የሚሰጥ ፈቃድ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ እስከ አንድ (1) አመት ድረስ የሚቆይ ይሆናል።

17. ፈቃድን ስለ ማሳደስ

በዚህ መመሪያ መሠረት የተሰጠ ፈቃድ የመጠቀሚያ ጊዜው ከማለቁ 15 (አስራ አምስት) ተከታታይ ቀናት በፊት መታደስ ይኖርበታል።

18. ፈቃድ ስለሚመለስበት እና ስለሚሰረዝበት ሁኔታ

18.1. በዚህ መመሪያ መሠረት ፈቃድ የተሰጠው አካል ሞተር ብስክሌቱን ለሌላ ወገን በስጦታ፣ በልውውጥ፣ በሽያጭ ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ ሲያስተላልፍ የወሰደውን ፈቃድ ለሰጠው አካል ፈቃዱን መመለስ አለበት።

18.2. ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ መሠረት የተጣለበትን ግዴታ ሲጥስ የተሰጠው ፈቃድ በፈቃድ ሰጪው አካል ሊሰረዝ ይችላል።

19. ፈቃድ የተሰጠው አካል ግዴታዎች

በዚህ መመሪያ መሠረት ፈቃድ የተሰጠውው አካል፣

19.1. ሞተር ብስክሌት በከተማው መንገድ ላይ ሲያንቀሳቅስ ፈቃዱን የመያዝ፣

19.2. ፈቃዱን እንዲያሳይ በትራፊክ ተቆጣጣሪ ወይም ስልጣን ባለው ህግ አስከባሪ ሲጠየቅ የማሳየት፣

19.3. ፈቃዱን ከተሰጠው አላማ ውጪ ያለመጠቀም፣

19.4. ፈቃዱን ለሌላ ሰው አሳልፎ ያለመስጠት፣

19.5. የድርጅቱን አርማ ያለበትን ሞተር ብስክሌት ብቻ የመጠቀም፣

19.6. የድርጅቱን የደንብ ልብስ ለብሶ የመንቀሳቀስ፣

19.7. በሪቬት የታሰረ ሰሌዳ የተለጠፈለትን ሞተር ብስክሌት ብቻ የመጠቀም፣

19.8. ፈቃዱ ቢጠፋ፣ ቢሰረቅ ስለ መጥፋቱ ወይም ስለ መሰረቁ በ48 ሰአት ውስጥ በአካባቢው ለሚገኝ የፖሊስ እና ፈቃድ ሰጪው አካል የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

20. የፈቃድ ሰጪው አካል ተግባርና ሃላፊነት

በዚህ መመሪያ መሠረት ፈቃድ ሰጪ አካል፣

20.1. ይህን መመሪያ ለማህበረሰቡ ተደራሽ በሆነ ሚዲያ የማስተዋወቅ፣

20.2. በዚህ መመሪያ መሠረት የሚሰጠው አገልግሎት ፈጣንና ቀልጣፋ እንዲሆን የማድረግ፣

20.3. በአጠቃላይ ይህን መመሪያ በተሟላ መልኩ ተግባራዊ የማድረግ፣

ተግባርና ኃላፊነት አለበት።

21. የትራፊክ ተቆጣጣሪ ተግባርና ኃላፊነት

21.1. የአሽከርካሪውን የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ተቀብሎ በመያዝ ለተቆጣጣሪ መስሪያቤት ያስረክባል፣

21.2. ትራፊክ ተቆጣጣሪ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች በመተላለፍ ጥፋት ሲፈፅም የተገኘን ሞተር ብስክሌት አሽከርካሪ በመያዝ ሞተር ብስክሌቱን በቁጥጥሩ ስር እንዲቆይ ያደርጋል።



City Government of Addis Ababa Road and Transport Bureau

22. የተከለከሉ ተግባራት

22.1. ፈቃዱን ከተፈቀደለት ሞተር ብስክሌት ውጭ አገልግሎት ላይ እንዲውል አሳልፎ መስጠት የተከለከለ ነው፣

22.2. ፈቃዱን መሰረዝ፣ መደለዝ ወይም አስመስሎ መስራት የተከለከለ ነው፤

22.3. የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈበት ፈቃድ መጠቀም የተከለከለ ነው፤

22.4. ፈቃድ ሳይዙ በከተማው መንገድ ላይ ሞተር ብስክሌት መንቀሳቀስ የተከለከለ ነው፣

22.5. ፈቃድን በፈቃዱ ላይ ላልተጠቀሰ ሌላ ሞተር ብስክሌት መጠቀም የተከለከለ ነው፣

22.6. የድርጅቱን አርማ ያልተቀባ ሞተር ብስክሌት በከተማው መንገድ ላይ ማሽከርከር የተከለከለ ነው፣

22.7. የድርጅቱን የደንብ ልብስ ሳይለብሱ በሞተር ብስክሌት በከተማው መንገድ ላይ መንቀሳቀስ ክልክል ነው፣

22.8. በሪቤት ያልታሰረ ሰሌዳ የተለጠፈለትን ሞተር ብስክሌት ማሽከርካር የተከለከለ ነው።

## ክፍል አራት

## ቅጣት ስለሚያስከትሉ የጥፋት ዓይነቶችና ስለቅጣት

23. ቅጣት ስለሚያስከትሉ የጥፋት ዓይነቶች

ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ድርጊቶች የፈፀመ አካል ቅጣት ይጣልበታል።

23.1. ፈቃድ ሳያወጡ ወይም አስመስሎ የተሰራ ፈቃድ ይዞ በከተማው መንገዶች ላይ በባለሁለት ጎማ ሞተር ብስክሌት መንቀሳቀስ፤

23.2. ጊዜው ያለፈበት ፈቃድ ይዞ በከተማው መንገድ ላይ መንቀሳቀስ፤

23.3. ፈቃዱን ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠት፤

23.4. የተሰረዘ ወይም የተደለዘ ወይም አስመስሎ የተሰራ ፈቃድ ይዞ መገኘት እና መጠቀም፤

23.5. ለሌላ ሞተር ብስክሌት የተሰጠ ፈቃድ እንደራስ አስመስሎ መጠቀም፤

23.6. በከተማው መንገድ ላይ እንዲንቀሳቀስ የተሰጠውን ፈቃድ ሳይዝ ሞተር ብስክሌት ማሽከርከር፤

23.7. የድርጅቱን አርማ ያልተቀባ ሞተር ብስክሌት በከተማው መንገድ ላይ ያሽከረከረ፤

23.8. የድርጅቱን የደንብ ልብስ ሳይለብስ በሞተር ብስክሌት በከተማው መንገድ ላይ የተንቀሳቀሰ፤

23.9. በሪቬት ያልታሰረ ሰሌዳ የተለጠፈለትን ሞተር ብስክሌት ያሽከረከረ፣

24. ቅጣት

24.1. በዚህ መመሪያ አንቀፅ **23** ንኡስ አንቀፅ **23.1.** የተቀመጠውን ጥፋት የፈፀመ ማንኛውም ሰው በወንጀል ህግ መሠረት ይቀጣል።

24.2. በዚህ መመሪያ አንቀፅ **23** ከንኡስ አንቀፅ **23.2.** እስከ **23.9.** የተዘረዘሩ የጥፋት አይነቶችን የፈፀመው ሰው ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ-1 መሠረት ይቀጣል።

ሰንጠረዥ- 1፡ *የቅጣት ሰንጠረዥ*፡፡

| ተ.ቁ | የጥፋት ዓይነት | የጥፋቱ ድግግሞሽና የቅጣት መጠን | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ለመጀመሪያ ጊዜ | ለሁለተኛ ጊዜ | ከሁለት ጊዜ በላይ |
| 1 | በከተማው መንገድ ላይ እንዲንቀሳቀስ የተሰጠውን ፈቃድ ሳይዝ ባለሁለት ጎማ ሞተር ብስክሌት ማሽከርከር፣ የድርጅቱን አርማ ያልተቀባ ሞተር ብስክሌት በከተማው መንገድ ላይ ያሽከረከረ ወይም የድርጅቱን የደንብ ልብስ ሳይለብስ በሞተር ብስክሌት በከተማው መንገድ ላይ የተንቀሳቀሰ እንዲሁም በሪቬት ያልታሰረ ሰሌዳ የተለጠፈለትን ሞተር ብስክሌት ያሽከረከረ፣ | 500.- | 1000.- | 2000.- ብር ተቀጥቶ ለሞተር ብስክሌቱ የተሰጠው ፈቃድ 3 ወር ይታገዳል፡፡ |
| 2 | ጊዜው ያለፈበት ፈቃድ ይዞ በከተማው መንገድ ላይ መንቀሳቀስ፣ የተሰረዘ ወይም የተደለዘ ወይም ፈቃዱን ለሌላ አካል አሳልፎ መስጠት እንዲሁም ለሌላ ባለሁለት መንኮራኩር ሞተር ብስክሌት የተሰጠ ፈቃድ እንደራስ አስመስሎ መጠቀም፣ | 750.- | 1000.- | 2000.- ብር ተቀጥቶ ለሞተር ብስክሌቱ የተሰጠው ፈቃድ ይሰረዛል፡፡ |

## ክፍል አምስት

## ስለ አቤቱታ

### 25. ስለአቤቱታ አቀራረብ

በዚህ መመሪያ መሠረት በተወሰደው እርምጃ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው፡-

25.1. እርምጃው በተወሰደ በ3 (ሦስት) የሥራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለባለስልጣኑ በፅሁፍ ለማቅረብ ይችላል፤ ከዚህ የጊዜ ገደብ ውጪ የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት አይኖረውም፤

25.2. ባለስልጣኑ አቤቱታው በቀረበለት በ3 (ሦስት) የስራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን መርምሮ ውሳኔ መስጠት አለበት፤ ውሳኔውንም በጽሁፍ ለአቤቱታ አቅራቢው ማሳወቅ አለበት፤

25.3. ባለስልጣኑ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው ወይም ቢሮው በ3 (ሦስት) የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሽ ካልሰጠው ባለስልጣኑ ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ወይም ውሳኔ መስጠት ከነበረበት ቀን አንስቶ በ5 (አምስት) የሥራ ቀናት አቤቱታውን ስልጣን ላለው አካል ማቅረብ ይችላል።

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**26. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ለዚህ መመሪያ ቀና አፈፃፀም የመተባበር ግዴታ አለበት።

**27. መመሪያ ስለማሻሻል**

አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ቢሮው ይህን መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው በማንኛውም ጊዜ ማሻሻል ይችላል።

**28. መመሪያዉ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ይህ መመሪያ ከሰኔ 30 ቀን 2011 ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ

ሰኔ 30 ቀን 2011ዓ.ም.

ሰለሞን ኪዳኔ ዘገየ (ፒ.ኤች.ዲ.)

የአዲስ አበባ ከተማ ኢኮኖሚ ክላስተር አስተባባሪና

የትራንስፖርት ቢሮ ሀላፊ

| የከተማ አስተዳደሩ አርማ | | የባለስልጣኑ አርማ |
|---|---|---|

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪኛ ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን**

**ሞተር ብስክሌት የከተማ ውስጥ እንቅስቃሴ ፈቃድ መስጫ ፎርም**

ፈቃዱ የተሰጠው ተቋም (ድርጅት) ሙሉ ስም፡- ______________________

አድራሻ፡-

ክልል፡- ______________ ከተማ፡- ______________________

ክፍለ ከተማ፡- ______________ ወረዳ፡- __________ የቤት ቁጥር፡-__________

የሞተር ብስክሌት ሰሌዳ ቁጥር፡- ______________________

የሻንሲ ቁጥር የሞተር ቁጥር፡- ______________________

የፈቃድ የአገልግሎት የተሰጠበት ቀን፡- ______________________

ፈቃዱ የሚያበቃበት ጊዜ፡- ______________________

**ፈቃዱን የሰጠው ኃላፊ ስምና ፊርማ**

______________________

**ማህተም**